# የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ

# 139ኛ ልዩ መግለጫ

**በዜጎች ላይ የሚፈጸም ሕገ-ወጥ ግድያ**
**በአስቸኳይ ይቁም!**

ጥቅምት 23 2008 ዓ.ም

አዲስ አበባ

ኢትዮጵያ

የምዝገባ ቁጥር 1146

www.hrco.org.et

ሰመጉ

## ዋናው ጽ/ቤት፡ አዲስ አበባ


አ.አ ስታዲየም አጠገብ ላሊበላ ሬስቶራንት ጎን፣ ሣኅለ ሥላሴ ሕንፃ 8ኛ ፎቅ፣ ቢሮ ቁጥር 19

ስልክ: (+251) 011 551-7704

ፋክስ: (+251) 011 551-7704

ኢሜይል: info@hrco.org.et

ድረ ገጽ: www.hrco.org.et

የፖስታ ሳጥን ቁጥር 2432

አዲስ አበባ፣ኢትዮጵያ


## የሰብዓዊ መብቶች ክትትል እና ምርመራ መምሪያ


ስልክ: (+251) 011 558-2387

ኢሜይል: monitoringcomplaints@hrco.org.et


## ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች


ሐዋሳ (ደቡብ ኢትዮጵያ ቀጠና): ስ.ቁ (+251) 046 220-4500፣ ፖ.ሳ.ቁ 360

ባሕርዳር (ሰሜን ኢትዮጵያ ቀጠና): ስ.ቁ (+251) 058 226-3913፣ ፖ.ሳ.ቁ 1115

ነቀምቴ (ምዕራብ ኢትዮጵያ ቀጠና): ስ.ቁ (+251) 057 661-5014፣ ፖ.ሳ.ቁ 463

ድሬደዋ (ምሥራቅ ኢትዮጵያ ቀጠና): ስ.ቁ (+251) 025 811 9150 ፖ.ሳ.ቁ 2596

ጅማ (ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ቀጠና): ስ.ቁ (+251) 147 211 5434

አዲስ አበባ (ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ቀጠና): ስ.ቁ (+251) 011 551-7704፣ ፖስታ ሳጥን ቁጥር 2432



የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ ★ Human Rights Council ★

# ማውጫ


1. የኢትዮጵያ አስተዳደር ክልል እና ዞን ካርታ ------------------ 1
2. የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ ----------------------------- ------ ---------------- 2
3. መግቢያ---------------------------------------------------------- 3
4. በሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በቀላፎና ሙስታሂል ወረዳዎች የተፈጸመ የሰብዓዊ መብት ጥሰት-------------------------------------- 3
   ሀ. የተገደሉ ሰዎች ስም ዝርዝር----------------------------- ----- 6
   ለ. በጦር መሣሪያ ማቁሰልና ድብደባ የተፈጸመባቸው ሰዎች ስም ዝርዝር -- -- 8
5. ማጠቃለያ ------------------------------------------------------------ 12
6. ማሳሰቢያ ------------------------------------------------------------ 12-14


የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ
Human Rights Council

# 1. የኢትዮጵያ አስተዳደር ክልል እና ዞን ካርታ[1]




የመብት ጥሰቱ የተፈጸመባቸው አካባቢዎች

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ Human Rights Council

[1] "ኢትዮጵያ" [ካርታ]. <http://www.h2empower.org/aboutus/factsethiopia.html>. (August 11, 2015)

## 2. የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ

የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ (ሰመጉ)፣ የቀድሞው የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ (ኢሰመጉ) በኢትዮጵያ የሽግግር ወቅት ቻርተር አንቀጽ 1(ሀ) እና በኢትዮጵያ ፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር ከ404-482 በተጻፉት ድንጋጌዎች መሠረት መስከረም 29 ቀን 1984 ዓ.ም. በአባላት የተመሠረተ የመጀመሪያው መንግሥታዊ ያልሆነ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋች ተቋም ነው፡፡ ሰመጉ በበጎ አድራጎትና ማኅበራት አዋጅ ቁጥር 621/2001 መሠረት "ኢትዮጵያዊ የበጎ አድራጎት ማኅበር" ሆኖ በምዝገባ ቁጥር 1146 በሕጋዊነት በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኝ ድርጅት ነው፡፡ ሰመጉ ከማናቸውም የፖለቲካ ፓርቲ፣ የኃይማኖት ተቋም፣ የብሔረሰብ ቡድን፣ ማህበራዊ መደብ ወዘተ የማይወግን፣ ለትርፍ ያልተቋቋመ፣ ነጻና ገለልተኛ የሆነ የሰብአዊ መብቶች ተከላካይ ተቋም ነው፡፡ ሰመጉ የቆመው ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መጎልበት፣ ለሕግ የበላይነት መስፈንና ለሰብዓዊ መብቶች መከበር ነው፡፡

ሰመጉ ላለፉት 24 ዓመታት በቆመላቸው ዐበይት ዓላማዎች ላይ በመመርኮዝ፣ ሁለንተናዊ ሐገራዊና ሕዝባዊ ተልዕኮ በመያዝ በነደፋቸው በርካታ የመርሐ-ግብር ተግባራት አማካኝነት ሰብዓዊ መብቶች እንዲከበሩ፣ የሕግ የበላይነት እና ሕጋዊ ሥርዓት እንዲሰፍንና በኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲኖር የበኩሉን አስተዋጽዖ በማበርከት ላይ ይገኛል፡፡

ዓበይት ዓላማዎቹንና ተልዕኮውን ለማሳካት ሰመጉ ፈርጀ ብዙ የሆኑ የመርሐ ግብር ተግባራትን ያከናውናል፡፡ ከነዚህም መካከል አንዱ በየደረጃው ለሚገኙ የመንግሥት አስፈጻሚ አካላትና ለሕዝብ የሰብዓዊ መብቶች ትምህርትና ሥልጠና መስጠት ነው፡፡ የመንግሥት አካላት በዋነኛነት የግዴታዎች ተሸካሚ፣ ሕዝብም በዋነኛነት የመብቶች ባለቤት እንደመሆናቸው መጠን፣ የመንግሥት አካላትም መብት የማክበርና የማስከበር ግዴታቸውን በዕውቀት፣ በችሎታና በጽኑ እምነት ላይ ተመርኩዘው እንዲወጡ፣ ሕዝብም እንዲሁ በዕውቀት፣ በችሎታና በጽኑ እምነት ላይ ተመርኩዞ መብቱን እንዲያስከብር ሰመጉ የሰብዓዊ መብቶች ትምህርትና ሥልጠና ይሰጣል፡፡

የሰመጉ መለያውና ግንባር ቀደም ተግባሩ በኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብቶችን አያያዝና ሁኔታ መከታተል፣ የሚፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ማጣራትና በማስረጃ የተደገፉ መግለጫዎችን ማውጣት ነው፡፡ ሰመጉ በሚያወጣቸው መግለጫዎች ሁሉ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ተጎጂዎች ፍትሕና ካሣ እንዲያገኙ፣ የጥሰት ፈጻሚዎች በሕግ እንዲጠየቁና ወንጀል ሠርቶ በነጻ መሄድ እንዲያበቃ፣ ከእያንዳንዱ ክስተት ትምህርት ተወስዶ ለወደፊቱ ጥንቃቄና እርማት እንዲደረግ ሲጮህና ሲጠይቅ ቆይቷል፣ አሁንም በመጠየቅ ላይ ነው፤ ለወደፊትም በዚሁ ይቀጥላል፡፡

በተጨማሪም በተለይ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት ሰለባ ለሆኑ ዜጎች የተለያየ ደረጃና መልክ ያለው የሕግ ድጋፍ መስጠት፣ በሰብዓዊ መብቶች ዙሪያ የጥናትና ምርምር ሥራዎችን ማከናወንና ውጤቶቹን በስብሰባዎችና በልዩ ልዩ የመገናኛ መንገዶች ማሠራጨትና የአድቮኬሲ ሥራዎችን መሥራት፣

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ
Human Rights Council

በመንግሥት የወጡና የሚወጡ ሕጎች ይዘትና አፈጻጸማቸውን መከታተል፣ የሕግ ታራሚዎችን መጎብኘትና ሰብዓዊ መብቶቻቸው መጠበቃቸውን መከታተልና የፍርድ ቤቶችን ሂደት መከታተል የሰመጉ ዋና ዋና ተግባራት ናቸው።

በእስካሁኑ ቆይታው ሰመጉ 36 መደበኛ መግለጫዎችና 138 ልዩ መግለጫዎችን በተጨማሪም በተለያዩ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ በርካታ ጋዜጣዊ መግለጫዎችን ይፋ አድርጓል። ሰመጉ አሁን በሚገኝበት አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ሆኖም ቢሆን፣ ሁኔታና ዐቅም በፈቀደለት መጠን የሰብዓዊ መብቶች መከበር፣ የሕግ የበላይነትና የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ በኢትዮጵያ እውን እንዲሆን ካለው የጸና ዓላማ አኳያ በመሥራት ላይ ይገኛል።

## 3. <u>መግቢያ</u>

ኢትዮጵያ የተቀበለችው ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች መግለጫ አንቀጽ 3 እያንዳንዱ ሰው በሕይወት የመኖር መብት እንዳለው ያረጋግጣል። ኢትዮጵያ ፈርማ የተቀበለችውና ፍጹም አስገዳጅ የሆነው የሲቪልና የፖሊቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳንም በአንቀጽ 6 ንዑሥ አንቀጽ 9 ላይ እያንዳንዱ ሰው በሕይወት የመኖር ተፈጥሮአዊ መብት እንዳለው ይደነግጋል። የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግሥትም ይህንኑ በሕይወት የመኖር መሠረታዊ መብት በአንቀጽ 15 ላይ ያረጋግጣል። በተጨማሪም ይህ መብት የማይደፈርና የማይገሠሥ መሆኑን የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 14 ይደነግጋል። ይሁን እንጂ ይህንን ሕገ መንግሥታዊና ዓለም አቀፋዊ ድንጋጌ በመተላለፍ በሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በቀላፎና ሙስታሂል ወረዳዎች ግድያ ተፈጽሟል።

## 4. <u>በሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በቀላፎና ሙስታሂል ወረዳዎች የተፈጸመ የሰብዓዊ መብት ጥሰት</u>

### ሀ. <u>ግድያ</u>

### <u>መግቢያ</u>


የሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በምሥራቅ ኢትዮጵያ የሚገኝ ክልል ነው። በክልሉ ውስጥ በርካታ ብሔር ብሔረሰቦችና የተለያዩ ጎሣዎች በጋራ ይኖራሉ። የገጠሩ ኅብረተሰብ ኑሮ የተመሠረተው በእርሻ፣ በከብት እርባታ እንዲሁም አትክልትና ፍራፍሬዎችን በማልማት ነው።

በክልሉ የሚኖሩ የሬርባሬና የዱቤ ጎሣዎች ከ1990 ዓ.ም ጀምሮ የማንነት ጥያቄ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት አቅርበዋል። ‹‹ባሕላችን፣ ቋንቋችን፣ የመኖሪያችን መልክዐ ምድራዊ አቀማመጥ ከሶማሌ ብሔረሰብ የተለየ በመሆኑ ልዩ ዞን እንዲሰጠን ጠይቀናል። ቀላፎ በቀዳማዊ ኃ/ሥላሤና በደርግ ዘመን አውራጃ ነበር። ቀላፎ ነባር አውራጃ ስለነበረ በአሁኑ ዞን እንዲሆን እስከ ጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ድረስ አመልክተናል።›› በማለት ይገልጻሉ።

የዱቤ እና የሬርባሬ ጎሣዎች ያቀረቧቸውን "የሰላም፣ የልማት፣ የዴሞክራሲና የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎች" ለመመለስ የዱቤና የሬርባሬ ሽማግሌዎች፣ የፌዴሬሽን ምክር ቤት ተወካይ፣ የሶማሌ ብ/ክ/መንግሥት ተወካዮች፣ የሙስታሂል ወረዳ ተወካዮች፣ የቀላፎ ወረዳ ተወካዮች፣ የፌርፌር ወረዳ ተወካዮች፣ የቀላፎ ወረዳ ተወካዮች፣ የምሥራቅ ኢሜ እና የምዕራብ ኢሜ ወረዳ ተወካዮች በተገኙበት

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ Human Rights Council

ሰኔ 21 ቀን 2004 ዓ.ም ጅግጅጋ ከተማ ላይ ኮንፍረንስ በማድረግ ባለ ስምንት ነጥብ የዐቋም መግለጫ አውጥተዋል፡፡




**የስብሰባው ተሳታፊዎች ያወጡት የዐቋም መግለጫ፡**

1. የዱቤ እና የሬርባሬ ጎሣዎችን በተመለከተ ይንጸባረቅ የነበረው ኋላ ቀር አመለካከትና ማኅበረሰቡን ዝቅ አድርጎ የማየት አስተሳሰብ የጎሣዎቹን አባላት ሥነ ልቦና የሚጎዳና የዴሞክራሲ መብቶችንም የሚፈታተን በመሆኑ ይህንን ኋላ ቀር አስተሳሰብ ከሥሩ ለመፈንቀልና የአስተሳሰብ ለውጥ ለማምጣት የሚያስችል ሥራ እንዲሠራ የተወሰነውን ውሳኔ ከልብ የምንደግፍ ስለሆነ ለተግባራዊነቱ የድርሻችንን ለማበርከት ቃል እንገባለን፡፡
2. የዱቤ እና የሬርባሬ ጎሣዎች ልጆች ለዘመናት ከትምህርት የተገለሉ ስለነበሩ መደበኛ ትምህርት ከማስፋፋት ጎን ለጎን በክልሉ አዳሪ ትምህርት ቤት አማካኝነት ለማኅበረሰቡ ልጆች ልዩ ትኩረት ተደርጎና በጀት ተመድቦ እንዲማሩ ለተደረሰው ስምምነት ተግባራዊነት ከመንግሥት ጎን በመቆም አስፈላጊውን ሁሉ ለማድረግ ቃል እንገባለን፡፡
3. የዱቤና የሬርባሬ ጎሣዎች በልማቱ እንዲሳተፉ እና የባለቤትነት መንፈስ ለማረጋገጥ እንዲቻል የጎሣውን አሠፋፈር ተከትሎ በክልልና በሌሎች የአስተዳደር የመንግሥት መዋቅር ውስጥ ሚዛናዊና ፍትሐዊ የሆነ ውክልና እንዲኖር የተላለፈው ውሳኔ ሕገ መንግሥታዊ መብታችንን ያረጋገጠ በመሆኑ ከልብ መቀበላችንን እናረጋግጣለን፡፡
4. ክልሉ የጤና፣ የትምህርት፣ የግብርናና የውኃ አቅርቦት ለማሻሻል ልዩ በጀት መድቦ እንዲሠራና አፈጻጸሙም ለፌዴሬሽን ም/ቤት ሪፖርት እንዲደረግ የተላለፈው ውሳኔ የሕዝባችንን የመልማት ጥያቄ የሚመልስ በመሆኑ ለተግባራዊነቱ አስፈላጊውን ሁሉ ለማድረግ ቃል እንገባለን፡፡
5. የሕዝባችንን በልማት ሥራ ላይ የታታሪነት መልካም ባሕል በመጠቀም በሚኖርበት አካባቢ በቂ የልማት ቦታና የማሥፈር ሥራዎች ተከናውነው የሕዝቡንና የክልሉን ልማት እንዲያሳልጥ በክልሉ በኩል ልዩ ድጋፍ እንዲደረግ የተላለፈው ውሳኔ የሕዝባችንን የልማት ተጠቃሚነት ይበልጥ የሚያረጋግጥ በመሆኑ ኅብረተሰባችንን በማስተባበር ውሳኔውን ተግባራዊ ለማድረግ ቃል እንገባለን፡፡

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ
Human Rights Council

6. የመሠረተ ልማት ለውጥ እስኪመጣ የሚያስፈልገውን የሰብዓዊ ዕርዳታ ለተቸገሩና ለተፈናቀሉ ወገኖች እንዲደረግ የተላለፈው ውሳኔ የኅብረተሰቡን ጊዜያዊ ችግር የሚፈታ በመሆኑ ከልብ የተቀበልነው መሆኑን እናረጋግጣለን፡፡
7. ከልዩ ልዩ ምክንያቶች ጋር በተያያዘ በእሥር ላይ የሚገኙ የማኅበረሰባችን ተወላጆች ለሰላምና ለእርቅ መሳካት ሲባል እንዲፈቱና ወደ ሰላማዊ ኑሯቸው እንዲመለሱ የተደረገውን ስምምነት ከልብ የተቀበልነው መሆናችንን እናረጋግጣለን፡፡
8. እኛ የዱቤ እና የሬርባሬ ጎሣዎች ከአጎራባች ጎሣዎችና ሕዝቦች ጋር በሰላም አብረን የምንኖርና ጥያቄውንም ሕጋዊና ሰላማዊ በሆነ መንገድ ስናቀርብ የነበርን ሲሆን፣ ወደፊት በአፈጻጸም ኺደትም አለመግባባቶች ቢከሰቱ በተለመደው ሰላማዊና ሕጋዊ መንገድ በውይይት የሚፈታበትን አግባብ ለመከተልና ተቀራርበን ችግሮችን ለመፍታት ዝግጁ መሆናችንን እናረጋግጣለን፡፡[2]

እኛ የኮንፍረንሱ ተካፋዮች የክልሉ መንግሥትና የፌዴሬሽን ምክር ቤት ያቀረቧቸውን የማግባቢያ ነጥቦች የተቀበልን ሲሆን፣ ተግባራዊ ለማድረግም ተስማምተናል፡፡ የሚል ስምምነት ተፈራርመዋል፡፡
የሰላም፣ የልማት፣ የዴሞክራሲና የመልካም አስተዳደር ኮንፍረንስ ተሳታፊዎች ባለ ስምንት ነጥብ የመግባቢያ ሠነድ በመቀበል ስምምነት ላይ ቢደረስም እስካሁን አንዱም እንዳልተፈጸመ ይገልጻሉ፡፡

በቀላፎ፣ ሙስታሂልና ፌርፌር ወረዳዎች ውስጥ ከሦስት መቶ ሺህ (300,000) የማያንሱ የሬርባሬ ጎሣ አባላት እንደሚኖሩ የአካባቢው ሽማግሌዎች ይገልጻሉ፡፡ ከአምሳ ሺህ (50,000) በላይ የሚሆኑ የዱቤ ጎሣ አባላት በምሥራቅ አሚ እና በምዕራብ አሚ ወረዳዎች ይኖራሉ፡፡ እንደ ሽማግሌዎቹ ገለጻ በቀላፎ ከዐሥር ዓመት በፊት በተከናወነው የሕዝብና ቤት ቆጠራ የሬርባሬ ጎሣ አባላት 121,000 (አንደ መቶ ሐያ አንድ ሺህ) የነበረ ሲሆን፣ የኦጋዴን ጎሳ አባላት ቁጥር ደግሞ 4000 (አራት ሺህ) ነበር፡፡ በጠቅላላው በወረዳው 125,000 (አንደ መቶ ሐያ አምስት ሺህ) ሕዝብ እንደሚኖር የአካባቢው የሀገር ሽማግሌዎች ይገልጻሉ፡፡ ዳሩ ግን የሬርባሬ ጎሣ አባላት ቋንቋቸውና ባሕላቸው ከኦጋዴን ጎሳ የተለየ ሆኖ ሳለ ወረዳውን የሚያስተዳድሩትና በመንግሥት ሠራተኛነትም ከፍተኛውን ቁጥር የያዙት የኦጋዴን ጎሣ አባላት እንደሆኑ ሽማግሌዎቹ በቅሬታ ይገልጻሉ፡፡ የሬርባሬና የዱቤ ጎሣዎች ሽማግሌዎች "የቀላፎ ወረዳ የቀድሞውን የአውራጃ ደረጃ በሚመጥን መልኩ ዞን እንዲሆን፣ እንደ ሌሎቹ ብሔር ብሔረሰቦች በቋንቋችንና በባሕላችን የመጠቀም መብታችንና የማንነት ጥያቄያችን ተከብሮልን ራሳችንን በራሳችን የማስተዳደር ሕገ መንግሥታዊ መብታችን እንዲጠበቅልን ጥያቄ አቅርበናል" በማለት ይገልጻሉ፡፡ ይህን ጥያቄ ለምን አነሣችሁ በማለት የሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ልዩ ፖሊስ ኃይል ታኅሣሥ 1 እና 2 ቀን 2006 ዓ.ም በፈጸመው አሠቃቂ የጅምላ ግድያ ከ65 ሰዎች በላይ የተገደሉ ሲሆን ከ153 በላይ ቆስለዋል፡፡ የሰመጉ ባለሙያዎች ድርጊቱ በተፈጸመባቸው ቦታዎች በአካል በመገኘት ጥቃቱ የተፈጸመባቸውን ዜጎችና ቤተሰቦቻቸውን በማነጋገር ድርጊቱ መፈጸሙን ለማረጋገጥ ችለዋል፡፡ በተጨማሪም ጉዳዩ ይመለከታቸዋል የተባሉትን የመንግሥት አካላት አግኝተው ምላሻቸውን ለማካተት ያደረጉት የተለያየ ጥረት አልተሳካም፡፡

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (ኢ.ፌ.ዲ.ሪ) ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 14 "ማንኛውም ሰው ሰብዓዊ በመሆኑ የማይደፈርና የማይገሰስ በሕይወት የመኖር፣ የአካል ደኅንነትና የነጻነት መብት" እንዳለው ይደነግጋል፡፡ በአንቀጽ 13/2/ ላይ እንደዚሁ "በዚህ ምዕራፍ የተዘረዘሩት የመሠረታዊ መብቶችና ነጻነቶች ድንጋጌዎች፣ ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ስምምነቶችና ሰነዶች ጋር በተጣጣመ መንገድ ይተረጐማሉ" በማለት ሠፍሯል፡፡ ኢትዮጵያ የተቀበለችው ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች መግለጫ አንቀጽ 3 እያንዳንዱ ሰው ነጻነቱና ደኅንነቱ ተጠብቆለት በሕይወት የመኖር መብት እንዳለው ይደነግጋል፡፡ ሌላው ኢትዮጵያ የተቀበለችው እና ፍጹም አስገዳጅ የሆነው የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳንም በአንቀጽ 6(1) ላይ የእያንዳንዱን ሰው በሕይወት የመኖር መሠረታዊ መብት ያረጋግጣል፡፡

[2] የዱቤና የሬርባሬ ማኅበረሰብ የሰላም፣ የልማት የዴሞክራሲና የመልካም አስተዳደር ኮንፈረንስ፣ ሰኔ 21 ቀን 2004፣ ጅግጅጋ ከተማ

## ታኅሣሥ 1 እና ታኅሣሥ 2 ቀን 2006 ዓ.ም የተገደሉ ሰዎች ስም ዝርዝር

| ተ.ቁ | የሟች ሙሉ ስም | የገደለው አካል | ተ.ቁ | የሟች ሙሉ ስም | የገደለው አካል |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ዑመር ሳግ መሐመድ | የክልሉ ልዩ ኃይል | 34 | ኢልሚ አብዲ ጉሬይ | ›› |
| 2 | ዊልየ አደዊ መሐመድ | ›› | 35 | ዐሊ አቦ ሀሬድ | ›› |
| 3 | ቀሊፍ መሐመድ አብዲ | ›› | 36 | ኢብራሂም በርሬ አሕመድ | ›› |
| 4 | ሐሰን ዐሊ ቤይሌህ | ›› | 37 | ሻምበል ሻፊ ዐሊ | ›› |
| 5 | መሐመድ ዐሊ ቤይሌህ | ›› | 38 | ዑመር አብዲ ገራድ | የክልሉ ልዩ ኃይል |
| 6 | ወ/ሮ አሾ ሐጅ መሐመድ | ›› | 39 | መሐመድኢብራሂም ቲሮው | ›› |
| 7 | መአሊም ዳልዩ ቶውሂድ | ›› | 40 | መሐመድ ኤርሴ የሮው | ›› |
| 8 | ሕፃን አብዲረሳስ አዳም መሐመድ | ›› | 41 | ዑመር ዩሱፍ አሬይ | ›› |
| 9 | ሕፃን ፋይ ኑር መሐመድ | ›› | 42 | ረጃ ዐሊ ደበን | ›› |
| 10 | ሕፃን ቦርዬ አሕመድ ብር | ›› | 43 | ጆሌ ዑመር አብዱላሂ | ›› |
| 11 | ሕፃን ገኦሉው አብዲ ዩሱፍ | ›› | 44 | አብድልፋህ ሐሰን አምጉሌ | ›› |
| 12 | ሕፃን ዩሱፍ ረሰስ አዳም | ›› | 45 | ባንሄድ ሐሰን አብዲ | ›› |
| 13 | ›› ሶሌባን ፊረህ ዑመርሂል | ›› | 46 | ኢብራሂም ሀጅ ኑር | ›› |
| 14 | ›› ዐሊ ዑስማን አብዲሴ | ›› | 47 | ወ/ሮ ማርየን ራጌ ሺኑርዬ | ›› |
| 15 | ›› ቀኒ መሐመድ አርሴ | ›› | 48 | ኢልሚ አቢ ሀሌድ | ›› |
| 16 | ›› ሙሴ መሐመድ ዐር | ›› | 49 | ዐርዬ በደይ ዶይ | ›› |
| 17 | ›› በደል ዐሊ ዑመርሂል | ›› | 50 | ኢሬ ሀሬድ ኑር | ›› |
| 18 | ካሚል መሐመድ አብደላ | ›› | 51 | መዴይ አብድ ኑር | ›› |
| 19 | ሶሐን በሌዩ አብዱላሂ | ›› | 52 | ሰንዊይኔ ሳሄድ ቡንሾይ | ›› |
| 20 | ዩሱፍ ጉሌይ ዐሊ | ›› | 53 | መሀመድ አዶ ቀሲንሌ | ›› |
| 21 | ፋራህ አዳል አሕመድ | ›› | 54 | ሼክ አብድየረ ቡንሾይ | ›› |
| 22 | መሐመድ ዐኪስማን ጉርበዕ | ›› | 55 | መአኔ አሪየ በዴይ | ›› |
| 23 | ሕፃን አሕመድ አብዲ ዐሊ | ›› | 56 | አቶ ፋራህ ዲሪየ | ›› |
| 24 | ዐሊ ቃሲም ቀሊንሴ | ›› | 57 | ዑመር አብድ ዶር | ›› |
| 25 | መሐመድ የሱፍ ኑር | ›› | 58 | ፊይሰል ኑር መሁመድ | ›› |
| 26 | አብዱላሂ አብዲ ወደቤ | ›› | 59 | ከሚል መሀሙድ ጀዳል | ›› |
| 27 | ዩሱፍ አብዱላሂ ዑመር | ›› | 60 | ዩሱፍ ሰሌባን አደን | ›› |
| 28 | ዋኔይ አሕመድ በርሬ | ›› | 61 | አብድስለል ሽቅለኔ ሀሬድ | ›› |
| 29 | መሐመድ ሁጃሌ ሐሰን | ›› | 62 | አህመድ ሙሁመድ ሙሴ | ›› |
| 30 | ሕፃን ኑር አብዲ ሰመድ | ›› | 63 | በደል ጋኒ ዑመርሂል | ›› |
| 31 | ›› ፋይ አሕመድ በደሌ | ›› | 64 | ዊሾ ደገኔ ጀዳል | ›› |
| 32 | ሁሴን ዑመር ዐሊ | ›› | 65 | ዩሱፍ አህመድ ሰሌባን | ›› |
| 33 | ደቡ ኑር አልሚ | ›› | | | |



ስም፡ ሕፃን ኑር አብዱሰመድ
ጾታ ፡ ወንድ
ዕድሜ፡ 8
ምርመራ፡ በልዩ ኃይል ፖሊስ በጥይት የተገደለ


የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ
Human Rights Council



ስም ፡ ሕፃን አህመድ አብዲአሊ
ጾታ ፡ ወንድ
ዕድሜ ፡ 4
ምርመራ ፡ በልዩ ኃይል ፖሊስ በጥይት የተገደለ



ስም ፡ ሕፃን አሊኡስማን አብደሌ
ጾታ ፡ ወንድ
ዕድሜ ፡ 5
ምርመራ ፡ በልዩ ኃይል ፖሊስ በጥይት የተገደለ



ስም ፡ አቶ ኡመር የሱፍ ኡሬሳ
ዕድሜ ፡ 40
ምርመራ ፡ በልዩ ሀይል ፖሊስ በጥይት የተገደለ

## ለ. በጦር መሣሪያ ማቁሰልና ድብደባ

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 16 ‹‹ማንኛውም ሰው በአካሉ ላይ ጉዳት እንዳይደርስበት የመጠበቅ መብት አለው›› ሲል ይደነግጋል። የሰዎች የአካል ደኅንነት የመጠበቅ መብት የማይደፈርና የማይገሠሥ መሆኑን የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 14 ያረጋግጣል። ይሁን እንጂ ይህንን ሕገ መንግሥታዊ ድንጋጌ በመተላለፍ የሚከተሉት ግለሰቦች በሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ልዩ ፖሊስ ኃይል ታኅሣሥ1 እና ታኅሣሥ 2 ቀን 2006 ዓ.ም በጥይት ተመትተው ለተለያዩ የአካል ጉዳቶች ተዳርገዋል።

<u>በሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በቀላፎ ወረዳ በተለያዩ ቀበሌዎች የአካል ጉዳት የደረሰባቸው ተጎጂዎች ስም ዝርዝር</u>


| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | የጎሣው ስም | የቀበሌው ስም | ጉዳት የደረሰበት የአካል ክፍል |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ዐሊ ኩን መካት | በጅማል | በአድ | ግራ ዓይን |
| 2 | አብዲ ዶፍ አብድላሂ አይሩክ | ›› | ›› | ግራ እግር |
| 3 | በሽር ኮድክ ብር | ›› | ›› | ግራ እግር |
| 4 | አርቴ መሐሙድ ኑር | ›› | ›› | ግራ እጅ |
| 5 | አብዲ መሐመድ ኑር | ›› | ›› | አፍ ላይ |
| 6 | ወ/ሮ የራዬ ኢቲ አብዱላሂ | ›› | ›› | ግራ ዓይን ጎን |
| 7 | ኦላት ዩሱፍ አደም | ›› | ›› | የቀኝ እግር ጭን |
| 8 | አህመድ ሪሄ መአልን | ›› | ›› | ግራ እጅ |
| 9 | አፍኮር ዐሊ መሀመድ | ›› | ›› | ግራ እግር |
| 10 | አህመድ ዩሱፍ ሽቅለሊ | ›› | ›› | ግራ እግር ጉልበት |
| 11 | ውቲን መቀዲን ሀሰን | ›› | ›› | ግራ እግር |
| 12 | ዩሱፍ ወየን ሙሐመድ | ›› | ›› | ግራ ጡት |
| 13 | አብዲ ኢድ አብዱላሂ | ›› | ›› | ግራ እግር |
| 14 | ዐሊ ሹካት ጁዶ | ›› | ›› | ግራ እጅ |
| 15 | ጉሀያት ሀቢ አብዲ | ›› | ›› | ግራ እጅ |
| 16 | ቦቤ ቃሁ መሀመድ | ›› | ›› | ግራ እግር ጉልበት |
| 17 | አብዲ ኢድ አብዱላሂ | ›› | ›› | ግራ እግር |
| 18 | ደራውሽ አብዲ ሲወን | ›› | ›› | ቀኝ እግር ተረከዝ |
| 19 | አብዲ ኢብራሂም ዑስማን | ›› | ›› | ቀኝ ጆሮ ተቆርጧል |
| 20 | ሼህ ሙሀዬ ሼክ ኢብራሂም | ›› | ›› | ግራ እጅ |
| 21 | ወ/ሮ ጉድዊይ አብዲከረም ወአዲ | ›› | ›› | ቀኝ እግር |
| 22 | እስማኤል ኢረት ሃጅ | ›› | ›› | ቀኝ ጎን አጥንት |
| 23 | አህመድ መሀት አደን | ›› | ›› | ቀኝ እግር |
| 24 | ዑመር አልካቤ ሀጅ | ›› | ›› | ቀኝ እጅ |
| 25 | ኑር ዩሱፍ ተውሂት | ›› | ›› | ግራ እግር |
| 26 | ወ/ሮ ፊናን አብዲ ሰበር | ›› | ›› | ግንባር ላይ |
| 27 | ›› ሁኔ እስማኤል ኡረት | ›› | ›› | ግራ እግር ጭን |
| 28 | ›› አስኒሮ ፋራ ሀሰን | ›› | ›› | ግራ እጅ |
| 29 | መሀመድ አልሞጎ መሀመድ | ›› | ›› | ግራ እጅ |
| 30 | ሽሂት ሀሰን አኖት | ›› | ›› | ግራ እግር |
| 31 | ወ/ሮ ኒዬ ዑመር ሼህ አደም | ›› | ›› | ጭንቅላት ላይ |
| 32 | ›› መርየም ኡጃሌ ሀርሲ | ›› | ›› | ግራ እግር |
| 33 | ከድል አብዲ ሂሬ | ›› | ›› | ግራ እግር |
| 34 | አደሞ ዳውድ ኢሉ | ›› | ›› | ግራ እጅ |
| 35 | ወ/ሮ ሮኮ ዑመር ሃሽ | ›› | ›› | ግራ ትከሻ |
| 36 | አህመድ ዴቆ ሲያት | በጅማል | በአድ | ግራ እግር |
| 37 | ወ/ሮ ሞጎ ሳዒድ አህመድ | ›› | ›› | ግራ እጅ |
| 38 | ዐሊ ጆር አብዲ ፋራህ | ›› | ›› | ቀኝ እጅ |
| 39 | በሽር መሀመድ ዴቆ | ›› | ›› | ቀኝ እግር ጭን |
| 40 | ራጌ ሾሬ ኑርዬ | ገሰር | ሞይኮ | ›› |
| 41 | አብዲ ረሽድ ኑር | ›› | ›› | ›› |
| 42 | በሬ ሀሰን ዳሒር | ›› | ›› | ›› |
| 43 | ገሬ ረሽድ ኢብራሂም | ›› | ›› | ግራ እግር |
| 44 | አብዱላሂ ዳኒ ተወኔ | ›› | ›› | ቀኝ እግር |
| 45 | አብዱ ከቡ አደኔ | ›› | ›› | ግራ እጅ |
| 46 | አደን ዴቅ ኩርጅ | ›› | ›› | ሆድ ላይ |
| 47 | አብዲ ሀኪን ቀሊሌ | ›› | ›› | ግራ እጅ |
| 48 | ሙሴ ጂብሪኢል አይናንሼ | ›› | ›› | ግራ እግር ተረከዝ |
| 49 | አብዲ ኢላሙን ሃጅ | ›› | ›› | ግራ እግር |

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ
Human Rights Council

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | የጎሣው ስም | የቀበሌው ስም | ጉዳት የደረሰበት የአካል ክፍል |
|---|---|---|---|---|
| 50 | አብዲ የሬሀሰን ኢማን | ›› | ›› | አንድ የዘር ፍሬ |
| 51 | አብደሌ ሀሰን ኢማን | ›› | ›› | ጆርባ ላይ |
| 52 | መሐመድ አባይሬ ሀሰን | ›› | ›› | ግራ እጅ ላይ |
| 53 | ፋራህ ኢብራሂም ዐሊ | ›› | ›› | ቀኝ ትከሻ ላይ |
| 54 | ኑር ኤልያስ ተወኔ | ›› | ›› | ጭንቅላት ላይ |
| 55 | ማን አብዱ ሁሴን | ›› | ›› | ›› |
| 56 | መሐሙድ ዐሊ መዑድ | ›› | ›› | ግራ ጎን አጥንት |
| 57 | ሙሽት አብዲቃሌ ዩሱፍ | ›› | ›› | ግራ እግር |
| 58 | ሻፋኢ ሀሰን ኑን | ›› | ›› | ግራ እጅ |
| 59 | ኢብራሂም ሼክ አህመድ ኑር | ›› | ›› | ቀኝ እግር ጭን |
| 60 | አብዲ ሱጌሳላት ዐሊ | ›› | ›› | ቀኝ እግር |
| 61 | ፉሩሌ ሀሰን ኢዩ | ›› | ›› | ቀኝ እግር ጭን |
| 62 | አብዲ ኡዱር ዐረብ | ›› | ›› | ቀኝ እግር ጭን |
| 63 | በሽር  አብድሌ ኑር | ›› | ›› | ቀኝ እግር ጭን |
| 64 | ሼክ ሙሴ ሴይሲ ፋራ | ›› | ›› | ጭንቅላት ላይ |
| 65 | ኡልሚ ሁሴን ሂሬ | ›› | ›› | ቀኝ እግር ተቆርጧል |
| 66 | መሀመድ ህርቤ ዐሊ | ›› | ›› | ›› |
| 67 | ሙሐመድ ዐሊ ሶስል | ›› | ›› | ቀኝ እግር |
| 68 | ዱሁል መሐመድ ደሬ | ›› | ›› | ›› |
| 69 | መሐመድ አህመድ ኑር | ›› | ›› | ቀኝ እግር ተረከዝ |
| 70 | አብዲ ራሞሌ ዐሊ | ›› | ›› | ጭንቅላት ላይ |
| 71 | ካህዬ ሞሉድ ህርሲ | ›› | ›› | ግራ እግር |
| 72 | ፈይሰን ቀየር አዴ | ›› | ›› | ቀኝ እግር |
| 73 | ወ/ሮ ፋጡም ቃሲም አምበር | ›› | ›› | ግራ እግር |
| 74 | ›› ጋአሮ አምበር ኢሴ | ›› | ›› | ግራ ዓይን |
| 75 | ሼክ ድሪዬ መሐመድ ሀሰን | ›› | ›› | ሁለት ጥርስ |
| 76 | አህመድ ቃሊፍ ሁሴን | ›› | ›› | ግራ እጅ |
| 77 | አብዲ መረክ መሐመድ | ›› | ›› | ›› |
| 78 | ወ/ሮ አረቦ ረሽድ እስማን | ገሰር | ሞይኮ | ግራ እግር |
| 79 | ዐሊ በሽር አብዲ | ›› | ›› | ግራ ጎን አጥንት |
| 80 | ዩሱፍ በሻ ዑስማን | ሬር ኢሴ | አፍዱብ | ቀኝ እግር ጭን |
| 81 | ቀሊፍ ገኒ ሀሰን | ›› | ›› | ግራ ጭን |
| 82 | ሚሴ ቲር አድን | ›› | ›› | ጀርባው ላይ |
| 83 | ሊሻን አህመድ ካር | ›› | ›› | ተረከዝ ላይ |
| 84 | አብዱ ሑቤ ፋራ | ›› | ›› | ግራ ጣት |
| 85 | ወ/ሮ ጅቡቲ መሐመድ ተወሌ | ›› | ›› | ጀርባ ላይ |
| 86 | ›› ፋጢም ተወኔ ሀሰኔ | ›› | ›› | ግንባር ላይ (በቀኝ በኩል) |
| 87 | ዐሊ ጉሌት ነገዬ | ›› | ›› | ግራ እግር |
| 88 | ኩምዬ ሙሴ | ›› | ›› | ወገብ ላይ (በግራ በኩል) |
| 89 | ቃሊፍ ዐሊ በሒ | ›› | ›› | ግራ ትከሻ |
| 90 | ሰኒይ ሁሜ መአሰን | ›› | ›› | ግራ እጅ ጣት |
| 91 | ወ/ሮ ምሞ ያቦይ ጀማል | ›› | ›› | ግራ እጅ |
| 92 | ብሌ አብዲ ዶሬ | ›› | ›› | ግራ ዐይን |
| 93 | ሼክ ኢባራሂ ሃጅ | ›› | ›› | ቀኝ እጅ |
| 94 | ኑጉስ ዐር መሐመድ | ›› | ›› | ጀርባ |
| 95 | ወ/ሮ ዳበት አብዱ ጉሬ | ›› | ›› | ጭንቅላት |
| 96 | መሐመድ መሐሙድ ኢርክ | ›› | ›› | ቀኝ እግር ጭን |
| 97 | ዐሊ ካቤ አልጎሬ | ›› | ›› | ግራ እጅ |
| 98 | በሽር ሀሰን ጉሀት | ›› | ›› | ቀኝ እጅ |
| 99 | ማንጋር ዐር መሐመድ | ›› | ›› | ብብት ላይ |
| 100 | አብዲቀየር በሾር ሀሰን | ›› | ›› | ቀኝ እግር |
| 101 | ሽሊኢ አንስ ዲጋር | ›› | ›› | ጀርባ |
| 102 | ሽዑር ሃጅ መሐመድ | ›› | ›› | ጭንቅላት ላይ |

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ
Human Rights Council

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | የጎሣው ስም | የቀበሌው ስም | ጉዳት የደረሰበት የአካል ክፍል |
|---|---|---|---|---|
| 103 | አሊሬ ዑስማን በሬ | ሬር ኢሴ | አፍዱብ | ወገብ ላይ |
| 104 | ጃማ መሐመድ ዲሎ | ›› | ›› | ግራ እጅ |
| 105 | መደቤ አስን ጎሬ | ›› | ›› | ግራ እግር |
| 106 | ዩሱፍ ሰሊማን ሀሰን | ›› | ›› | ቀኝ እግር ከጉልበት በታች ተቆርጧል |
| 107 | ውሊ አጋስ ድጋሌ | ›› | ›› | ግራ እግር |
| 108 | ሄትጉል ጉሬ ድጌ | ›› | ›› | ግራ እግር ጭን ላይ |
| 109 | ወ/ሮ አደይ ሰብሪዬ ኑር | ›› | ›› | ቀኝ ጎድን አጥንት ላይ |
| 110 | ወ/ሮ ፊሀን ኢሴ ዩኑስ | ›› | ›› | ቀኝ ጭን |
| 111 | ወ/ሮ አስኒኖ ዑመር አልሚ | ›› | ›› | ጭንቅላት ላይ |
| 112 | አህመድ ሙሐመድ አብዲ | ›› | ›› | ግራ እጅ |
| 113 | ዐሊ ቢደል ሀሰን | ›› | ›› | ግራ ጉንጭ |
| 114 | ወ/ሮ ዳህሎ መሐመድ አብዲ | ›› | ›› | ተረከዝ ላይ |
| 115 | ሼክ ጋቦ አረብ ሁሴን | ›› | ›› | ግራ እጅ |



ስም ፡ አቶ ሙሀመድ ኡርሲ
ዕድሜ ፡ 55
ምርመራ ፡ በልዩ ሀይል ፖሊስ በጥይት ቀኝ እጃቸውን እና የቀኝ ሽንጣቸውን የተመቱ



ስም ፡ አቶ አያሽ ድሪር በድይ
ዕድሜ ፡ 50
ምርመራ ፡ በልዩ ኃይል ፖሊስ በጥይት ቀኝ እጃቸውን የተመቱ



ስም ፡ አቶ አብዱልቃድር ቀንሌ
ዕድሜ ፡ 76
ምርመራ ፡ በልዩ ኃይል ፖሊስ በጥይት ግራ እጃቸውን የተመቱ

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ
Human Rights Council

በሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሬርባሬ ጎሣ ተወላጆች ላይ ግድያና ማቁሰል ከመፈጸሙ በተጨማሪ ግምቱ 15 ሚሊዮን ብር የሚገመት እህል ከአውድማና ከማሳ ላይ ተቃጥሏል። የ150 አባወራዎች መኖሪያ ቤቶች ተቃጥለዋል። ይህንን ችግር ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት፣ ለኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን፣ ለሐገር መከላከያ ሚኒስቴር፣ ለፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር፣ ለፌዴሬሽን ም/ቤት፣ ለሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ በተደጋጋሚ ማመልከታቸውን በመስክ ሥራ ላይ ለተገኙ የሰመጉ ባለሙያዎች የተጎጂዎች ተወካዮች በምሬት ገልጸዋል።

ችግሩ በተከሰተበት አካባቢ የተገኙት የሰመጉ ባለሙያዎች ባሎቻቸው የተገደሉባቸውን ሴቶች፣ ልጆቻቸው የተገደሉባቸውን ወላጆች፣ ወንድሞቻቸው የተገደሉባቸውን ሰዎች አነጋግረዋል። እንዲሁም፣ የቆሰሉትንና የአካል ጉዳት የደረሰባቸውን ሰዎች አነጋግረዋል፤ የደረሳባቸውንም ጉዳት ተመልክተዋል።



በሱማሌ ክልል ልዩ ኃይል ፖሊስ የአካልና የንብረት ጉዳት ከደረሰባቸው ዜጎች መካከል ጥቂቶቹ



በሱማሌ ክልል ልዩ ኃይል ፖሊስ ባሎቻቸው የተገደሉባቸውና የንብረት ጉዳት ከደረሰባቸው ዜጎች መካከል ጥቂቶቹ

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ
Human Rights Council

## 5. ማጠቃለያ

በዚህ የሰመጉ 139ኛ ልዩ መግለጫ ሕገ ወጥ ግድያ፣ በአካል ላይ ጉዳት ማድረስ፣ የንብረት ውድመትና የቤት ቃጠሎ መፈጸሙን ሰመጉ ለማጣራት የቻለው ከቀረቡለት አቤቱታዎች በመነሣት ድርጊቶቹ ወደተፈጸሙበት አካባቢ ባለሞያዎችን በመላክ ባሰባሰበው ማስረጃ ነው፡፡ ከዚህ መግለጫ መረዳት የሚቻለው የሐገራችን የሰብዓዊ መብቶች ሁኔታ አሳሳቢ ሁኔታ ላይ የሚገኝ መሆኑን ነው፡፡ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቱ የተፈጸመው በመንግሥት ባለሥልጣናትና የጸጥታ ኃይሎች መሆኑ ደግሞ ሁኔታውን እጅግ አሳሳቢ ያደርገዋል፡፡ ስለሆነም መንግሥት የሐገሪቱን ሕገ መንግሥት እንዲያከብር ሰመጉ ይጠይቃል፡፡

**በተጨማሪም፡-**

- መንግሥት ለጉዳዩ ልዩ ትኩረት በመስጠት ሕገ ወጥ ግድያ፣ አካል የማጉደል፣ ንብረት የማውደምና ቤት የማቃጠል ወንጀል የፈጸሙትን የጸጥታ ኃይሎች ሕግ ፊት እንዲቀርቡና ወንጀሉ እንዲፈጸም ትዕዛዝ የሰጡ ባለሥልጣናትም በሕግ እንዲጠየቁ እንዲያደርግ፣
- ከሕግ ውጭ የተገደሉ ዜጎች ቤተሰቦች፣ በግፍ የአካል ጉዳት የደረሰባቸው ተጎጂዎች፣ ንብረታቸው የወደመባቸውና መኖሪያ ቤቶቻቸው የተቃጠሉባቸው ተጎጂዎች ሁሉ ተገቢውን ካሣ የሚያገኙበትን መንገድ መንግሥት እንዲያመቻች፣
- በሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በጅግጅጋ ከተማ ሰኔ 21 ቀን 2004 ዓ.ም በተዘጋጀው የሰላም፣ የዴሞክራሲና የመልካም አስተዳደር ኮንፍረንስ ላይ የፌዴሬሽን ም/ቤት፣ የሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥትና የሁሉም ወረዳዎች ተወካዮች ያወጡትንና የተስማሙበትን ባለ ስምንት ነጥብ የጋራ ስምምነት ተግባራዊ የሚሆንበትን መንገድ መንግሥት እንዲፈልግ ሰመጉ ይጠይቃል፡፡

ለሰብዓዊ መብቶች መከበርና ለሕግ ልዕልና የቆማችሁ ዜጎች፣ ብሔራዊና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች፣ የመንግሥታትና የዓለም አቀፍ ድርጅቶች ተወካዮች፣ መንግሥት ለሰብዓዊ መብቶች መከበርና ለሕግ ልዕልና መረጋገጥ አስፈላጊውን የሕግና የተቋማት ዝግጅት እንዲያደርግና ለእውነተኛ ተግባራዊነታቸውም በቂ ትኩረት ይሰጥ ዘንድ ከዚህ በታች ለተጠቀሱት የመንግሥት አካላትና ባለሥልጣናት በመጻፍ እንድታሳስቡ ሰመጉ ጥሪውን ያቀርባል፡፡

## 6. ማሳሰቢያ

ዜጎች እንዲሁም ሐገር አቀፍና ዓለም አቀፍ ተቋማት መንግሥት የዜጎችን ሰብዓዊ መብቶችን እንዲያከብር፣ እንዲያስከብርና፣ ለመብቶቹ መከበር ወሳኝ የሆኑ ቅድመ ሁኔታዎችን እንዲያሟላ ከዚህ በታች በተገለጹት አድራሻዎች በመጻፍ ጥያቄና ግፊት እንድታደርጉ ሰመጉ ይጠይቃል፡፡

- **ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት**
  ፖ.ሳ.ቁጥር ፡- 80001፣ ኢ-ሜል፡- national.parliament@telecom.net.et፣
  ፋክስ ፡- (+251) 011 155-0400፣የስልክ ቁጥር ፡- (+251) 011 124-1000፣
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
- **ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፌደሬሽን ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት፡-**
  ፖ.ሳ.ቁጥር ፡- 20122/1000፣ ኢ-ሜል ፡- kumashih@gmail.com
  ፋክስ ፡- (+251) 011 124-1208/011 124-2308፣
  የስልክ ቁጥር ፡- (+251) 011 122-3322፣
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ Human Rights Council

- **ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፕሬዝዳንት ጽ/ቤት:-**
  ፖ.ሳ.ቁጥር:- 23698፣ ፋክስ :- (+251) 011 551- 8656፣
  የስልክ ቁጥር:- (+251) 011 551-8186፣
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

- **ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት :-**
  ፖ.ሳ.ቁጥር:-1031፣ ፋክስ:- (+251) 011 122-6292፣
  የስልክ ቁጥር:- (+251) 011 124-1155፣
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

- **ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ጽ/ቤት:-**
  ፖ.ሳ.ቁጥር:- 5608፣ ኢ-ሜል:- mofatr1@yahoo.com፣
  ፋክስ:-(+251)011 551-1200፣
  የስልክ ቁጥር:-(+251) 011 515-3204፣
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

- **ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፍትሕ ሚኒስቴር ጽ/ቤት:-**
  ፖ.ሳ.ቁጥር:- 1370፣ ኢ-ሜል: justabr@ethionet.et፣
  ፋክስ:- (+251) 011 551-7775፣
  የስልክ ቁጥር:- (+251) 011 551-3620፣
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

- **ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም:-**
  ፖ.ሳ.ቁጥር:- 2459፣ ኢ-ሜል: ombudsmaneth@ethionet.et፣
  ፋክስ:- (+251) 011 553-2073፣
  የስልክ ቁጥር:- (+251) 011 543-336፣
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

- **ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን:-**
  ፖ.ሳ.ቁጥር:- 1165፣ ኢ-ሜ: hrcom@ethionet.et፣
  ፋክስ: (+251) 011 550-4125፣
  የስልክ ቁጥር:- (+251) 011 550-4031፣
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

- **ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፌደራል ፖሊስ ዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት:-**
  ፖ.ሳ.ቁጥር:- 199፣ የስልክ ቁጥር:- (+251) 011 551-2744፣
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

- **ለሶማሌ ክልል ም/ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:-**
  ፖ.ሳ.ቁጥር 392፣ ፋክስ:- (+251) 25 775-3429፣
  የስልክ ቁጥር: (+251) 257 75 34 29
  ጅግጅጋ፣ ኢትዮጵያ

- **ለኦሮሚያ ክልል ም/ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:-**
  ፖ.ሳ.ቁጥር:- 101769፣ ኢ-ሜል:- oromiawiev@ethionet.et፣
  ፋክስ:- (+251) 011 551-3642 / (+251) 011 551-9633፣
  የስልክ ቁጥር:- (+251) 011 552-4247፣
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

- **ለደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ም/ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:-**
  ፖ.ሳ.ቁጥር:- 1546፣ ፋክስ:- (+251) 046 220-2408፣
  የስልክ ቁጥር:- (+251) 046 221-4778/ 046 220-5848፣
  ሐዋሳ፣ ኢትዮጵያ

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ
Human Rights Council

- **ለቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ም/ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:-**
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 44፣ ፋክስ፡- (+251) 057 775-0814፣
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 055 7775-0109፣
  አሶሳ፣ ኢትዮጵያ

- **ለአማራ ክልል ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:-**
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 1324፣ ፋክስ፡- (+251) 058 220-2511፣
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 058 220-2659፣
  ባሕርዳር፣ ኢትዮጵያ

- **ለትግራይ ክልል ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:-**
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 291፣ ፋክስ፡- (+251) 034 441-6564፣
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 034 441-6563፣
  መቀሌ፣ ኢትዮጵያ

- **ለጋምቤላ ክልል ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:-**
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 25፣ ፋክስ፡- (+251) 046 220-2408፣
  ጋምቤላ፣ ጋምቤላ

- **ለሐረሪ ክልል ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:-**
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 952 ፋክስ፡- (+251) 025 666-2530፣
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 025 666-1723 / 025 666-1746
  ሐረር፣ ኢትዮጵያ

**[illegible]**